
# የ2014 ህዝብ ቆጠራ ሙከራ

## *ለ2020 የሕዝብ ቆጠራ በዝግጅት ላይ*




### ዋሺንግተን ዲሲ እና ማንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ

የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ የ2014ቱን የሕዝብ ቆጠራ ሙከራ የሚያደርገው በዋሽንግተን ዲሲ፣ እና ማንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ነው፡፡ የሙከራው ቦታ ወደ 200,000 የሚጠጉ ቤቶችን ያካትታል፡፡ የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ሙከራውን ለማድረግ በዳውንታውን ሲልቨርስፐሪንግ፣ ሜሪላንድ ውስጥ ጊዜያዊ የአከባቢ የሕዝብ ቆጠራ ጽህፈት ቤት ከፍቷል፡፡

ለበለጠ መረጃ **census.gov**

ስለ ሥራ ቅጥር መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ በ1-888-480-1639 ይደውሉ፡፡

የዩ.ኤስ. ሕዝብ ቆጠራ ቢሮ ሕዝቡ በ2020 በሚደረገው የሕዝብ ቆጠራ ላይ የመቆጠር ህዝባዊ ግዴታውን እንዲወጣ የሚረዱ ዘመናዊ እና ገንዘብ ቆጣቢ የሆኑ ዘዴዎችን በማጥናት ላይ ይገኛል፡፡ በኢንተርኔት በኩልም ይሁን በስልክ ወይም በተለመደው በወረቀት መልክ የተዘጋጁ መጠይቆች፣ የሴንሰስ ቢሮ በየአስርቱ ዓመት ግዴታ መደረግ ያለበት ሄድካውንት (ውስን የሕዝብ ቆጠራ) ሁሉንም እንዲያሳትፍ ፈጣን፣ ቀላል እና አስተማማኝ ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም አለው፡፡

ቴክኖሎጂን እና አሁን ያሉት የመንግስት የዳታ ምንጮችን በብልህነት በመጠቀም፣ በ2020 የሚካሄደው የህዝብ ቆጠራ ጥራት እና ትክክለኛነት ላይ ያለውን ቁርጠኝነት ከማስቀጠልም ባሻገር ግምት የሚሰጠው የግብር ከፋይ ቁጠባ ለማስገኘት ይሻል፡፡ የ2014ቱ የሙከራ ሕዝብ ቆጠራው የሕዝብ ቆጠራ ቢሮ የተለያዩ አዳዲስ ዘዴዎችን፣ በመጨረሻ ላይ ደግሞ በ2020 የሚደረገው የህዝብ ቆጠራ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታሰቡ ስልጡን ቴክኖሎጂዎችን በተወሰነ መልኩ ለመሞከር ያስችለዋል፡፡ ሙከራው ከሰኔ እስከ መስከረም 2014 ይካሄዳል፡፡

## የ2014ቱ የሙከራ የሕዝብ ቆጠራ ዓላማ

- ኢንተርኔትን በመጠቀም ራስን ችሎ የመመለስ አቅም እንዲጨምር ለማድረግ እና በወረቀት መጠይቆች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ የተለያዩ ዘዴዎችን መሞከር፡፡
- ለጥራት ያለን ቁርጠኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሙከራው የህዝብ ቆጠራ ላይ ባልተሳተፉ ቤተሰቦች ላይ የክትትል ዳታ የመሰብሰቢያ ዘዴዎችን ማሻሻል።

## ግቦች

- የ2014ቱ የሙከራ ሕዝብ ቆጠራ ግዜ ሲደርስ አንዳንድ ቤተሰቦች ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስችላቸው በኢሜይል ወይም በቴክስት መልእክት እንዲነገራቸው እንዲመዘገቡ ለማድረግ፡፡
- በኢንተርኔት የሚሰጡ ምላሾችን ለማበረታታት እና ለመጨመር፡፡
- ለፈጣን ዳታ ቅንብር የሚያገለግል በስማርት ስልክ የሚገኝ አውቶማቲክ መሳርያ በመጠቀም ምላሽ ለማይሰጡ ቤተሰቦች የሚደረግ የዳታ ማሰባሰብ ሂደት ማሻሻል፡፡

## ለጊዜያዊ የአከባቢ የሕዝብ ቆጠራ ጽህፈት ቤት ሰራተኛ መቅጠር

| ሥራ አስኪያጆች | ደሞዝ/በሰዓት | የጀመሩበት እና የጨረሱበት ቀን* |
|---|---|---|
| የአከባቢ የሕዝብ ቆጠራ ጽህፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ (1) | $29.22 | 3/10–10/31/14 |
| የፊልድ ኦፐሬሽንስ ረዳት ሥራ አስኪያጅ (1) | $24.72 | 3/10–10/31/14 |
| የአስተዳደር ረዳት ሥራ አስኪያጅ (1) | $21.47 | 3/10–10/31/14 |
| የቴክኖሎጂ ረዳት ሥራ አስኪያጅ (1) | $21.47 | 3/10–10/31/14 |
| የቢሮ ኦፐሬሽን ሱፐርቫይዘሮች (2) | $15.41 | 4/07–10/31/14 |

| በ2014 የሚደረገው የሕዝብ ቆጠራ ሙከራ ክፍት የሥራ ቦታ | ደሞዝ/በሰዓት | የጀመሩበት ቀን* |
|---|---|---|
| የፊልድ ኦፐሬሽን ሱፐርቫይዘር (8) | $21.50 | 6/12/14 |
| ቡድን መሪዎች (65) | $20.00 | 7/02/14 |
| ቡድን ረዳት መሪዎች (104) | $18.50 | 7/21/14 |
| ቆጣሪዎች (800) | $18.50 | 7/21/14 |

*ቀናት ተቀራራቢ ግምት ናቸው

United States Census Bureau
U.S. Department of Commerce
Economics and Statistics Administration
U.S. CENSUS BUREAU
census.gov
DN-530/14(A)